# ስማችን --- ኢወክንድ
# ልሳናችን---- ነቅንቅ

ግንቦት 2002 ዓም

## በዘር መከፋፈል አምባገነን ስርዓትን ያጠናክራል

ለአይን የሚያስጠይፍ ፤ ልጅሮ የሚስቀጥጥ ፤ አፍንጫ የሚስነፍጥ፤ አገር የሚያስጠፋ፤ ትውልድ የሚያስመትር ከድንቁርናና ከራስ ወዳድነት ብሎም ከባዕድ ቅጥረኝነት ከሚወለዱ በሽታዎች ሁሉ እንደ ዘረኝነት የከፋ የለም ።

ባለፉት አስራ ዘጠኝ የወያኔ መርገምት ዓመታት ታሽተንበታልና ፤ ተንገላተንበታልና ፤ ትኩሱ ጉልበታችን ተዳክሞበታልና ፡ ለዚህም ነው ወግድ ጎጠኝነት ብለን ኢትዮጵያን ለማዳን ኢትዮጵያን አስቀድመን ኢወክንድ የሆንነው ። በኢሕኣፓ ወጣቶች ክንፍ ድርጅት ጥላ የተሰባሰብን የትውልድ አደራ ተረካቢዎች የነጻነትን ትርጉም እድሜ ለቀደምቶቻችን ተረድተነዋልና በአንድነት በኢትዮጵያዊነት ተደራጅቶ መታገልን የመሰለ ባርነትን መላቀቅያ አቀራጭ ጎዳና ከቶውንም የለምና በዘር በሃይማኖት በፆታ በክልል መከፋፈል በወጣቱ ቋንቋ ጤባ አመጣሽ ዘይቤ ብለነዋል ።

ኢትዮጵያን ከካርታ ሕዝቦዋን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ከዘመናት ጠላቶቿዋ ቀብድ በልቶ የሚንደፋደፈው የወያኔ ሥርዓት እኛ ወጣቶቹን እንዳናበር በዘር፤ ለሃገር እንዳናሰብ በክልል፤ እንዳንግባባ በቋንቋ ከፋፈሎና ሸንሽኖ አሥራ ዘጠኝ ቀን መቀመጥ የማይገባው ገለባ ስራዓት አሥራ ዘጠኝ ዓመት ላያችን ላይ ተቆጠረብን ። በእውነት አፍረናል ።

መሬቱን ገለባ ያርግላቸውና ስመ ጥሩዎቹ የኢትዮጵያ ወጣቶች የአፍሪካ የትግል ቀንዲል የነበሩ የኢትዮጵያ ተማሪዎች የከፈሉት ክብርና ንሁዱ መስዋትነታቸው የከፈሉ በኢትዮጵያዊንት እንጂ ከቶውንም በዘረኛነት አልነበረም። ከተማሪው መሪ ጥላሁን ግዛው እስከ ወጣቱ ባቢሌ ኃ/ሥላሴ ከስራተኛዋ ዳሮ ነጋሽ እስከ ተማሪዋ መነን ኃይሉ፤ ከሙደስር ኡስማን እስከ እጅጋየው ደበላ ከነገመቹ እስክ አሕፈሮም ሃብተ ስላሤ ወዘተረፈ....

ከኤርትርያ ትግራይ፤ ከጎንደር ጎጃም፤ ከሲዳሞ ባሌ ፤ከሐረር ጋምቤላ፤ ከስድስት ኪሎ አራት ኪሎ፤ ከልዑል መኮንን እስተ ተፈሪ መኮንን ከደሴው ወይዘሮ ሲህን እስክ አዳማው አፄገላውዲዮስ፤ ከጅማው ሚያዘያ ሃያ ሰባት እስከ ሐረሩ መዳኔ ዓለም ሁለተኛ ፤ ተማሪዋች የትግላቸው መነሻና መድረሻ ኢትዮጵያ ነበረች ። ዲሞክራሲም ነበር መፈክራቸው ። ታዲያ እነዚህ ትንታግ ቀደምቶቻችን በቅለው በረገፉባት ምድር ፤ ባፈሰሱት ደማቸው ላይ ቆመን የዘንድሮ የስድሰት ኪሎ ተማሪዎች የወያኔ ዘረኛ ፖሊሲ ስለባ ሆነን በዝር ተከፋፍለን መጋደል ነበረብን? ይህ ለኢትዮጵያ ተማሪዋች በሙሉ የቀረበ የስብዕና ጥይቄ ነው ። እኛ ኢወክንዶች ወያኔ አፈራሽ የዘረኝነት በሽታ ተላላፊ ሆኖ እርስ በርሰ ለተፋጁና ሰለባ ለሆኑት ሃዘናችንን ብንገልጽም ከሃዘኑ በላይ መሪር ሃዘን የሆነብን የቀደምቶቻችን የኢትዮጵያ ተማሪዎች የአንድነት ትግል ታሪክ ላይ ቆሻሻ ጠባሳ መጣሉ ነው ።

በዘር መከፋፈል በሎም ደም መፋሰስ ጠቀሜታው ነፃነቱን በወያኔዎች ለተገፈፈው ሕዝባችን ሳይሆን ለራሱ ለገፋፊው ሥርዓት ነውና ይህ ትግል ሳይሆን ከንቱ ልፊያና በከንቱ የፈሰሰ የጅል ደም ብለነዋል ። ወያኔ በትግራይ ሕዝብ ስም የተደራጀ ሰይጣን ሥርዓት እንጂ ለትግራይ ሕዝብ የመጣ እንዳልሆነ ሁሉ ለኦሮሞም ለአማራውም ለሌላውም የማይበጅ መሆኑን እንደኛ ተረድታችሁ እራሳችሁን በኢወክንድ ሆነ በሌላም ተደራጅታችሁ በዚህ

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: join@eprpy.com
www.eprpy.com

በከረፋና በቁሙ በሞተ ሥርዓት አፍንጫ ሰር ትግላችንን ማጠጣፍ ሲገባን ቁልቁል የካሮት አይነት እድገት ተከትለን መከፋፈልና መጨርሰ የባርነት ስንሰለታችንን ያጠብቀው ይሆን እንጂ አያላላውምና ለአገራችን ነፃነት ለአንድነታችንና ለእድገታችን ደንቃራ ሆኖ የሚያውከን የወያንኔ ሥርዓት መሆኑን ተገንዝበን መታገል ሲገባን ወያኔ በጋተን የዘረኝነት መርዝ ፋፍተን ደም መፋሰሰ ኢወክንድ ያፈረብትና ያዘነበት መሆኑን በአፅኖት ይገልጻል ።

በመጨረሻም ጥሪ ለኢትዮጵያ ወጣቶች በሙሉ

በልዩነታችን ላይ ሳይሆን በአንድነታችን ላይ የተማከል ትግል እንጂ ወያኔ ባጋተን የዘረኝነት መርዝ መሳከርና መጨረስ ተራፊ የለውምና ይህንን የአሥራ ዘጠኝ ዓምት የጨለማ ጉዞ በአንድነት አብረን ለኢትዮጵያ ብርሃን መሆን አለበን ነው የመጨረሻ ጥሪያችን።

ኢትዮጵያዊ ከሆናችሁ፤ ዘረኝነት ከኮነናችሁ የወያኔ ሥርዓት የሕዝብና የታሪክ ጠላት መሆኑን ተረድታችሁ ይህንን ሥርዓት ለማስውገድ ከቆረጣችሁ በያላችሁበት ኢወክንድ ናችሁና የመንፈስ ቁርኝነታችንን አጠንክረን በስልትና ወጣታዊ ቅልጥፍና አካላዊ ትስስራችንን አጠናክረን በኢትዮጵያዊነት ኩራት ዘርኝነት የሰበረውን መንፈሳችንን እንደምናጠናክርና በጋራ ለጋራ ሃገራችን የትንሳዬን መዝሙር የምንዘምርበት ቀን ሩቅ አይሆንም እንላለን ።

ዘረኝነት ይሰብራል

ኢትዮጵያዊነት ያብባል

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣቶች ክንፍ ድርጅት

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: join@eprpy.com
www.eprpy.com